# የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት
# የሥነሥርዓት መመሪያ ቁጥር
# 807/2013

## መግቢያ

በሀገራችን ውስጥ የሚታዩትን የድህነት ቅነሣና ኢኮኖሚ ዕድገት ግስጋሴ ለማፋጠን ከሚረዱ ቁልፍ ተግባሮች መካከል የከፍተኛ ትምህርት ዕድገት አንዱ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በዚህ ረገድ ከሽግግር ጊዜ ጀምሮ በወጡ የመንግስት ፖሊሲዎች አዋጆችና ድንጋጌዎች የግሉ ዘርፍ በከፍተኛ ትምህርት ኢንቨስትመንት ውስጥ እንዲሣተፍ በመፍቀዱ በመጀመሪያዎቹ ዓመታት ከነበሩት በጣት የሚቆጠሩ ተቋማት በአሁን ወቅት ቁጥራቸው ከ170 የሚበልጥ የግል ተቋዋማት በዘርፉ ተሰማርተው የበኩላቸውን አስተዋፅኦ እያደረጉ ይገኛሉ፡፡

በአሁኑ ወቅት የግሉ ዘርፍ ለመንግስት የድህነት ቅነሣና የኢኮኖሚ እድገት ፖሊሲዎች ከሚያበረክተው አስተዋፅኦ በተጨማሪ ለዜጎች ተጨማሪ ዕድሎችን በመክፈት ሃገሪቷ በሰው ሃይል ግንባታ ረገድ የምታደሪውን ጥረት በከፍተኛ ሁኔታ እያገዘ ይገኛል፡፡ ይህ ዘርፍ ወደፊት ዕድገት እንዲያስመዘግብና ከህዝብና ከመንግስት የሚጠበቅበትን ሃላፊነት በተሻለ ቁመና እንዲወጣ ለማስቻል መንግስት በተለያየ ጊዜ ዘርፉ የሚመራባቸውን መርሆዎችና የአሠራር ዘይቤዎች ሲተልም ቆይቷል፡፡ በዚህ ረገድ አዋጅ ቁጥር 650/2001 እንዲሁም በከፍተኛ ትምህርት ጥራትና አግባብነት ኤጀንሲ በተከታታይ የተዘጋጁ መመሪያዎችና ደንቦችን መጥቀስ ይቻላል፡፡

ይህ መመሪያ በየጊዜው በዘርፍ የሚታዩ ዕድገቶችንና ሁኔታዎችን በመገንዘብ የተዘጋጀ ነው፡፡

መመሪያው በአራት ክፍሎች የተከፈለ ሲሆን በመጀመሪያው ክፍል ጠቅላላ ድንጋጌዎችን ይዟል፡፡ በክፍል ሁለት ሊጠበቁ የሚገባቸው አጠቃላይ የስነምግባር መርሆዎች የተዘረዘሩ ሲሆን በክፍል ሶስት ዋና ዋና ድንጋጌዎች ሰፍረዋል፡፡ በአራተኛው ክፍል ላይ ማጠቃለያ ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች ይገኛሉ፡፡ የመመሪያው አጠቃላይ መንፈስ አዎንታዊ ሲሆን ይህም በዘርፉ የሚታየው እንቅስቃሴ ለህግ የተገዛ የተቋማት እንቅስቃሴም ጤናማና የስከነ እንዲሆን የራሱን ድርሻ ያበረክታል ተብሎ ይታመናል፡፡

## ክፍል አንድ

### ጠቅላላ ድንጋጌዎች

#### ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጓሜ የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ፡-

1) ‹‹አዋጅ›› ማለት የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 ነው፡፡
2) ‹‹ሚኒስቴር›› ማለት የሳይንስና ከፍተኛ የትምህርት ሚኒስቴር ነው፡፡
3) ‹‹ሃላፊ›› ማለት የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተርና ምክትል ዋና ዳይሬክተር ማለት ነው፡፡
4) ‹‹የከፍተኛ ትምህርት›› ማለት በስነጥበብ ማሕበራዊ ሳይንስ በሳይንስና ቴክኖሎጂ መስኮች በቅድመ ምረቃና ድህረ ምረቃ የዲግሪ ፕሮግራሞች በአዋጅ ቁጥር 650 / 2001 አንቀጽ 19 ስር በተመለከቱት የትምህርት አግባቦች የሚሰጥ ትምህርት ማለት ነው፡፡
5) ‹‹ኤጀንሲ›› ማለት የከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ ማለት ነው፡፡
6) ‹‹ተቋም›› ማለት የግል የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና በርቀት ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ የተሰማሩ የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ማለት ነው።
7) ‹‹የዕውቅና ፈቃድ›› ማለት በከፍተኛ ትምህርት ስልጠና ለመጀመር በአዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 76 መሰረት ለተቋም የሚሰጥ የስራ ፈቃድ ነው፡፡
8) ‹‹የዕውቅና ፈቃድ እድሳት›› ማለት በአዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 80 መሰረት ለተቋም የሚሰጥ የዕውቅና ፈቃድ ዕድሳት ማለት ነው፡፡
9) ‹‹ካምፓስ›› ማለት አንድ ተቋም ትምህርትና ስልጠና ለመስጠት ፈቃድ ያገኘበት ህነጻ ወይም ስፍራ ማለት ነው።
10) ‹‹ዋና ማስተባበሪያ ማዕከል ማለት›› አንድ በርቀት ትምህርትና ስልጠና መንገድ የተሰማራ ወይም ለመሰማራት ከኤጀንሲው ፈቃድ የጠየቀ ተቋም ትምህርትና ስልጠናውን ለመምራት ያደራጀው ዋና ማዕከል ማለት ነው።
11) ‹‹ቅርንጫፍ ማዕከል›› ማለት የዋና ማስተባበሪያ ማዕከል ቅርንጫፍ ማለት ነው።
12) ‹‹መጋቢ ወይም ሳተላይት ጣቢያ›› ማለት በቅርንጫፍ ማዕከል ስር የሚገኙና ውስን የርቀት ትምህርት አገልግሎቶችን በመስራት ቅርንጫፍ ማዕከሉን የሚደግፉ ጣቢያዎች ማለት ነው፡፡
13) ‹‹የደረጃ ስያሜ›› ማለት በአዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 9 መሰረት በሚኒስቴሩ ለተቋማት የሚሰጥ ዩኒቨርሲቲ፤ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ፤ ኮሌጅ፤ ኢኒስቲቲዩት ማለት ነው፡፡
14) ‹‹ምርምር›› ማለት በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በቡድን ወይም በግል የሃገሪቱን እና የማህበረሰቡን ችግሮች በመለየት ወይም ልዩ የመፍጠር አቅምን በመጠቀም ተጨባጭና ሳይንሳዊ ውጤት ወይም የመፍትሄ አቅጣጫ ለማስቀመጥ የሚያስችል የጥናትና ምርምር ስራ ማለት ነው፡፡

15) ‹‹የትምህርት ፕሮግራም›› ማለት በመስኩ ሰልጥኖ ላጠናቀቀ ምሩቅ የመጀመሪያ ዲግሪና ከዚያ በላይ የሆነ የትምህርት ማስረጃ ሊያሰጥ የሚችል የትምህርት መስክ ማለት ነው።

16) ‹‹ሃላፊነት ማለት›› በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650 / 2001 አንቀጽ 95 መሰረት የወጡ ደንቦች፤ መመሪያዎች፤ ድንጋጌዎችን ተላልፎ የተገኘ ተቋም የሚያስከትልበትን የፍትሐብሔርና የወንጀል ሃላፊነት ማለት ነው፡፡

17) ‹‹ህጋዊ እርምጃ›› ማለት በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 እና ይህንን ለማስፈጸም ከኤጀንሲው የወጡ ማናቸውምንም መመሪያዎችን ተላልፎ በተገኘ ተቋም ላይ ሊከተል የሚችል ቅጣት ማለት ነው።

## ዓ ላ ማ

የዚህ መመሪያ ዓላማ የግል የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እንቅስቃሴ ህጋዊ መሰረት እንዲኖረው ማገዝ፣ ከህግ ማዕቀፍ ውጭ የሚደረጉ ማናቸውንም ተግባራት መከላከል፣ በተቋማት መካከል ጤናማ ውድድር መፍጠር እና ተጠያቂነት በማስፈን ዘርፉ የተሻለ እድገት እንዲኖረው መርዳት ነው፡፡

## የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ ለማስተማር በተቋቋሙ የመንግስት እና የግል የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## የኤጀንሲው ግዴታዎች

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ይህንን መመሪያ እንዲያውቁት ማድረግና መፈጸም እንደ አስፈላጊነቱም ትምህርትና ስልጠና በመስጠት የመመሪያውን አፈጻጸም መከታተል ናቸው፡፡

## የኤጀንሲው ስልጣንና ተግባር

ኤጀንሲው በአዋጅ ቁጥር 650/2001 እና በደንብ ቁጥር 261/2004 መሰረት የተዘረዘሩት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

## ክፍል ሁለት

## አጠቃላይ የስነምግባር መርሆዎች

ተቋማት በዚህ ክፍል ውስጥ የተመለከቱትን አጠቃላይ የስነምግባር መርሆዎች እንዲያከብሩና እንዲፈጽሙ የሚጠበቅ ሲሆን ይህ ባልሆነበት ሁኔታ አስፈላጊው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ይደረጋል፡፡

### 2.1 ሕግን ማክበር

ህግን ማክበር ማለት የህግ የበላይነትን በመቀበል ማናቸውንም ተቋማዊ ተግባር በህግና ህግ በሚፈቅደው መሰረት ብቻ ማከናወን ማለት ነው፡፡ በመሆኑም ተቋማት፡-

1. ህገ መንግስቱንና የሃገሪቱን ህጎች የማክበርና የማስከበር እንዲሁም አግባብነት ባላቸው የከፍተኛ ትምህርት አዋጆች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ ፖሊሲዎች፣ የማስፈጸሚያ ቼክ ሊስቶች፣ ስልጣን ባላቸው ሃላፊዎች በሚሰጡት ትዕዛዞች መሰረት ግዴታቸውን መወጣት አለባቸው፡፡
2. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሃላፊዎች ህገወጥ ወይም ተገቢ ያልሆነ መመሪያ ወይም ትዕዛዝ ለተቋማት ከማስተላለፍ መቆጠብ ይኖርባቸዋል::

### 2.2 ተጠያቂነት

ተጠያቂነት ማለት ማንኛውም የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ለሚሰራው ስራ፣ ለሚያስተላልፈው ውሳኔና ለሚሰጠው ማስረጃ እንዲሁም ለሚወስደው እርምጃ ሃላፊነት መውሰድን ይመለከታል፡፡ በመሆኑም ተቋማት፡-

1. የመንግስትን ፖሊሲ ጠብቀው መስራት ሲኖርባቸው ፖሊሲውን ተላልፈው በተገኙ ጊዜ ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡
2. ተቋማት ለሚሰጧቸው ውሳኔዎች፣ ለሚሰጡት ማስረጃ እንዲሁም ለሚያከናውኗቸው ተግባራት ሁሉ ሀላፊነት ይወስዳሉ፡፡
3. ተቋማት ግዴታቸውን በአግባቡ ስለመወጣታቸው ጥያቄ ሲቀርብላቸው አስፈላጊውን ማብራሪያና መረጃ መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡ በተፈለገ ጊዜና ቦታም የመቅረብ ወይም የመገኘት ግዴታ አለባቸው፡፡

### 2.3 ሐቀኝነት

ሀቀኝነት ማለት ለራስ፣ ለሕዝብ፣ ለሕግና ስራው ለሚጠይቀው ምግባር ታማኝና ብቁ ሆኖ መገኘትን ይመለከታል፡፡ በመሆኑም ተቋማት፣

1. ለህዝብ የገቡትን ቃል የማክበር፣ ቅን የመሆን፣ ከማታለልና ህገወጥ ድርጊት ከመፈጸም ወይም በሙስናና በመደለያ ጉዳዮችን ከማስፈጸምና ከመፈጸም የጸዱ መሆን አለባቸው፡፡
2. ለኤጀንሲው ትክክለኛና ያልተዛባ መረጃ ማቅረብ ይገባቸዋል፡፡
3. የመንግስትን ሃብትና አገልግሎቶችን ፍትሃዊ በሆነ መንገድ መጠየቅና መስተናገድ ይኖርባችዋል፡፡
4. ከሐቀኝነት በራቀ ስነምግባር የህዝብን ጥቅም በሚጎዳ መልኩ ከመስራት መታቀብ ይኖርባቸዋል፡፡

## 2.4 ግልጸኝነት

ግልጸኝነት ማለት ለህብረተሰቡና ለኤጀንሲው ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ እንዲደርሰው ማድረግን ይመለከታል፡፡ በመሆኑም ተቋማት፣

1. ህግን በማይቃረን ሁኔታ መንቀሳቀስ፣ ውሳኔዎችና ማስረጃዎችን በግልጽ ለሚመለከታቸው አካላት ማሳወቅና ለውሳኔአቸው ህጋዊ ምክንያት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ አስፈላጊ ሲሆንም ለሚያሳልፉት ውሳኔ ተገቢውን ማብራሪያ መስጠት ይጠበቅባቸዋል
2. የሚሰጡት አገልግሎት ህዝባዊ እንደመሆኑ መጠን ከተገልጋዮች ለሚቀርብላቸው የመረጃ ጥያቄ መረጃው በሚስጥር እንዲጠበቅ በህግ የታዘዘ ካልሆነ በስተቀር ምላሽ መስጠት አለባቸው፡፡
3. በግምገማ ሂደት ወይም በድንገተኛ ጉብኝት ወቅት ገምጋሚ ቡድኑ ለሚያቀርበው የመረጃ ጥያቄ በወቅቱ ምላሽ መስጠት አለባቸው፡፡

## 2.5 ቅንነት

ቅንነት ማለት ጠንካራ ዕምነት፣ ጽኑ አቋምና ሃቀኝነትን የሚያሳይ ስብዕና ማለት ነው፡፡ በመሆኑም ተቋማትና ሰራተኞቻቸው፣

1. ጥሩ ስነምግባር በማሳየት ስራቸውን በስርዓት፣በቅንነትና በብቃት መስራት ይኖርባቸዋል፡፡
2. ለሙያቸውና ለስራቸው ጠቃሚ የሆኑ አስተያየቶችንና አሰራሮችን ከተገልጋዮቻቸውና ከባለድርሻ አካላት በቅንነት በመቀበል ለመማርና ግልጋሎቶቻቸውን ለማሻሻል ዝግጁ መሆን አለባቸው፡፡
3. ህግን ተከትለው በተሰጣቸው ፈቃድ ብቻ ስራን ማከናወንና ተገቢ ያልሆነ አድራጎት ከመፈጸም መቆጠብ አለባቸው፡፡
4. ከተማሪዎችና ከኤጀንሲው ጋር የስራ ግንኙነት በሚያደርጉበትና ሙያዊ ግልጋሎት በሚሰጡበት ወቅት የተገልጋዮቻቸውን እምነት በሚጠብቅና በተቋማቸው ላይ ዕምነት በሚያሳድር መልኩ መሆን ይኖርበታል፡፡

Federal Democratic Republic of Ethiopia Higher Education Relevance & Quality Agency

## 2.6 ታማኝነት

ታማኝነት ማለት ለተቋቋሙበት አላማ፣ ህጎችና ደንቦች እንዲሁም ለተቋማቸው ታማኝ መሆንን ያመለክታል፡፡ በመሆኑም ተቋማት፣

1. ህገመንግስቱን የማክበርና የማስከበር፣ ለኤጀንሲው ህጎችና ለተማሪዎቻቸው ታማኝ የመሆን፣ ስራቸውን በህግ፣ በደንብና በመመሪያ መሰረት ብቻ ማከናወን ይኖርባቸዋል
2. በተቋማቸውም ሆነ በሌሎች አቻ ተቋማት ውስጥ የትምህርት ስርዓቱን የሚጎዳ ህገወጥ ድርጊት መፈጸሙን ሲመለከቱ ወዲያውኑ እርምጃ መውሰድ እንደ አስፈላጊነቱም ለኤጀንሲው መረጃ በመስጠት ህገወጡ ድርጊት እንዲቆም ማድረግ አለባቸው፡፡

## 2.7 ምስጢር መጠበቅ

ምስጢር መጠበቅ ማለት ይፋ እንዲወጡ ያልተፈቀዱ መረጃዎችን ያለማውጣትን ይመለከታል፡፡ በመሆኑም ተቋማት፣

1. በስራ አጋጣሚ ያወቋቸውንና በምስጢር ሊጠበቁ የሚገባቸውን ወይም መንግስታዊ የሆኑ መረጃዎችን በሚስጥር መያዝ አለባቸው፡፡
2. በህግ ካልተፈቀደ በስተቀር በስራ አጋጣሚ ያወቋቸውን ምስጢሮች መግለጽ የለባቸውም፡፡
3. በሕግ ወይም ሕጋዊ አካላት ካልተጠየቀ በስተቀር የተማሪን መረጃ አሳልፎ መስጠት የለባቸውም፡፡
4. ተቋማት ስራ ቢያቆሙም በስራ አጋጣሚ ያወቁትን ሃገራዊ መረጃ የመጠበቅ ግዴታ አለባቸው፡፡
5. ምስጥራዊ ያልሆነ ወይም ህዝቡ የሚያውቀውን ወይም ሊያገኘው የሚገባውን መረጃ መደበቅ የለባቸውም፡፡

## 2.8 የህዝብን ጥቅም ማስቀደም

የህዝብን ጥቅም ማስቀደም ማለት ማንኛውንም ተግባር የህዝብን ፍላጎት መሰረት በማድረግ ማከናወንና የጋራ ጥቅምን ማስቀደምን ይመለከታል፡፡ በመሆኑም ተቋማት፣

1. የሚሰጧቸው ውሳኔዎችና የሚያከናውኗቸው ስራዎች የህዝቡን ጥቅም እንጂ የግላቸውን ወይም የወዳጆቻቸውን ወይም የሌላ አካልን ጥቅም የሚያስቀድሙ መሆን የለባቸውም፡
2. ከሚሰጧቸው ውሳኔዎችና ከሚያከናውኗቸው ስራዎች ጋር በተያያዘ የጥቅም ግጭትን ለመፍጠር የሚችሉ ሁኔታዎችን አስቀድሞ ለኤጀንሲው ወይም ለሚመለከተው አካል ማሳወቅ/መግለጽ ይጠበቅባቸዋል፡፡

3. ከመደበኛ የመማር ማስተማር ስራ ጋር የሚጋጭ ሌላ ስራ በተቋሙ ስም መስራት የለባቸውም፡፡

## 2.9 ስልጣንን በአግባቡ መጠቀም

ስልጣንን በአግባቡ መጠቀም ማለት በህግ ተወስኖ የተሰጠን ስልጣን በመጠቀም ሃላፊነትን መወጣትን ይመለከታል፡፡ በመሆኑም ተቋማት፣

1. ከሚያከናውኗቸው የመማር ማስተማር ስራ ጋር በተያያዘ ያላቸውን የመወሰን ስልጣን በህግ ተወስኖ በተሰጠ መብት መሰረት ብቻ ተግባራዊ ማድረግ አለባቸው፡፡ በሕግ ከተሰጠ ስልጣን ውጭ ተቋማት በስልጣናቸው ያለአግባብ መገልገል አይችሉም፡፡
2. ተቋማት በስልጣናቸው ተጠቅመው በማስገደድ ወይም ተጽዕኖ በመፍጠር ተገልጋዮቻቸውን ህግ ከሚሰጣቸው ነፃነት ውጭ መጠቀሚያ ማድረግ የለባቸውም፡፡
3. ተቋማት ህግን መሰረት በማድረግ ብቻ ሚዛናዊ የሆነ ውሳኔ መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡

## 2.10 አድሎ አለመፈጸም

አድሎ አለመፈጸም ማለት ተማሪዎችን፣ ተገልጋዮችንና ተቋማትን በእኩል ደረጃ ማየትንና ልዩነት ያለመፍጠርን የሚያመላክት ነው፡፡ በመሆኑም ተቋማት፣

1. ተገቢና ፍትሃዊ በሆነ አኳኋን ውሳኔ የመስጠትና ስራቸውን በመመሪያና በደንብ መሰረት የማከናወን ግዴታ አለባቸው፡፡
2. በቀለም፣ በዘር፣ በብሄር፣ በጾታ፣ በቋንቋ፣ በኃይማኖት፣ በፖለቲካ አመለካከት ወይም በሌላ አቋም ወይም አግባብነት በሌለውግ ምትምክንያት የተለየ አድልዎ ሳይፈጥሩ ወይም ልዩነት ሳያደርጉ ተገልጋዮቻቸውን ማስተናገድ ይጠበቅባቸዋል፡፡
3. በሌሎች መሰልና አቻ ተቋማት ላይ ጥላቻ እንዲፈጠር ከመሞከርና የነዚህኑ ተቋማት ስም፣ ክብርና ስራ ከሚያጎድፍና ከሚጎዳ ድርጊት መቆጠብ ይኖርባቸዋል፡፡

## 2.11 ለህዝብ ጥያቄ ተገቢውን ምላሽ መስጠት

ለህዝብ ጥያቄ ተገቢውን ምለሽ መስጠት ማለት ህዝብን በአክብሮት ማገልገልን የሚያመለክት ነው፡፡ በመሆኑም ተቋማት፣

1. ተማሪዎቻቸውንና ተያያዥ ባለጉዳዮቻቸውን በጥሞና ማዳመጥና ችግሮቻቸውን ለመፍታት መጣር ይገባቸዋል፡፡
2. ተቋማት ተገልጋዮቻቸው ለሚያቀርቧቸው ጥያቄዎቻቸው በወቅቱ ተገቢውን ምላሽና መፍትሄ መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ
Federal Democratic Republic of Ethiopia Higher Education Relevance & Quality Agency

## 2.12 አርአያነት

አርአያ መሆን ማለት በመልካም ስነምግባር ለሃገርና ለዜጎች አብነት በመሆን ግልጋሎት መስጠትን ይመለከታል፡፡ ስለሆነም ተቋማት፣

1. የመማር ማስተማር ስራን በሚያከናውኑበት ማህበረሰብ ውስጥ ግንባር ቀደምና ምሳሌ በመሆን የሚጠበቅባቸውን ከፍያለ አርአያነት በማሳየት ማህበረሰብ አቀፍ ስራዎችን በማጎልበት በተግባር እንዲያገለግሉ ይጠበቃል፡፡
2. ሃላፊነት የሚሰማቸው፣ የተሻለ ለውጥን የሚደግፉና የተቋማቸውን መልካም ስም የሚጠብቁ፣ ህግ የማክበር ባህል እንዲዳብር፣ መተማመን ስር እንዲሰድና ጸንቶ እንዲቆይ የሚያደርጉ ሠራተኞች ሊኖሯቸው ይገባል፡፡

# ክፍል ሶስት

## የተከለከሉ ተግባራትና የሚያስከትሉትን ቅጣት የሚያመለክቱ ድንጋጌዎች

### አንቀፅ 1

ከኤጀንሲው ፈቃድ ሳያገኝ ማስተማር የጀመረ ተቋም ፡-

1.1. ተቋሙ እንዲዘጋ ይደረጋል፡፡

1.2. ተቋሙ ያለፍቃድ ስራውን ሲያከናውን በቆየባቸው መስኮች የሰጠው ትምህርት ወይም ማስረጃ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

1.3. ተግባሩን የፈፀመው ተቋም እና ባለቤት ወደፊት በማናቸውም መልኩ በእውቅና ፈቃድ ሂደት ውስጥ እንዲካተት አይደረግም፡፡

1.4. ኤጀንሲው ተቋሙን በተመለከተ የወሰደውን እርምጃ አስመልክቶ ለህዝቡ በሚዲያ ያሳውቃል፡፡

1.5. ህገወጥ ተግባሩን የፈፀመው ተቋም በአገሪቱ የወንጀልና የፍትሐብሔር ሕግ ይጠየቃል፡፡

### አንቀፅ 2

ፈቃድ ባልተገኘበት ካምፓስ ስልጠና መስጠት

2.1. በመደበኛው ኘሮግራም "ቅርንጫፍ ካምፓስ" ተብሎ የሚገለጸው እውቅና ከተገኘበት ከዋናው የተቋሙ መቀመጫ ከሶስት መቶ (300) ሜትር ራዲየስ ውጭ የሆነ ሲሆን ለእንዲህ ዓይነቱ ቅርንጫፍ ካምፓስ ማንኛውም ተቋም የእውቅና ፈቃድ ከኤጀንሲው መጠየቅ ይኖርበታል፡፡ ከዚህ ውጭ የሚደረግ ስልጠና ህጋዊ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

2.2. በርቀት ትምህርት አሰጣጥ ስልት ዋና ማዕከል ተብሎ የሚገለጸው የእውቅና ፈቃድ የተገኘበት ተቋም ዋና መስሪያ ቤት በተጨማሪ በሃገሪቱ የተለያዩ ክፍሎች በቅርጫፍነት የተቋቋሙና በስራቸው ተጠሪ ጽ/ቤቶች ሊኖራቸው የሚችሉ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ናቸው፡፡ ማንኛውም ተቋም ለእነዚህ ቅርንጫፎች ጽ/ቤቶች የእውቅና ጥያቄውን አቅርቦ ፍቃድ ማግኘት ሲኖርበት በእነዚህ ጽ/ቤቶች ስር የሚገኙ መጋቢ ወይም ሣተላይት ጣቢያዎችንም በተመሳሳይ ለኤጀንሲው ጥያቄ በማቅረብ እውቅና ማገኘት ይኖርባቸዋል፡፡ ከዚህ ውጭ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ህጋዊ ተቀባይነት አይኖራቸውም፡፡

ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን ድንጋጌዎች ተላልፎ የተገኘ ተቋም

2.1.1. ካምፓሱ ወይም የርቀት ቅርንጫፍ ማዕከሉ እንዲዘጋ ይደረጋል።

2.2.2. ካምፓሱ ወይም የርቀት ቅርንጫፍ ማዕከሉ ያለፍቃድ ስልጠና ሲሰጥበት በቆየው የትምህርት ፕሮግራም የተሰጠው ትምህርትና የት/ማስረጃ በማንኛውም መልኩ ተቀባይነት አይኖረውም

2.2.3. ተቋሙ በዚያ ከተማ ወይም አካባቢ ለ-3 ዓመታት በከፍተኛ ትምህርት መስክ እንዳይሰማራ እግድ ይጣልበታል፡፡

2.2.4. በተማሪዎች ላይ ለሚደርሱ ማናቸውም ጉዳቶች ድርጊቱን የፈጸመው ተቋም ሙሉ በሙሉ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

2.2.5. በአዲስ ካምፓስ ወይም የርቀት ቅርንጫፍ ማዕከል ለመሥራት የዕውቅና ፍቃድ የሚጠይቁ ተቋማት በሚኖሩበት ወቅት ኤጀንሲው በህግ በተደነገገው የግዜ ገደብ መሰረት ተቋሙ ላቀረበው የእውቅና ፈቃድ ጥያቄ ምላሽ መስጠት አለበት፡፡

2.2.6. ከተቋሙ አቅምና ዕቅድ ውጪ የካምፓስ ወይም የርቀት ቅርንጫፍ ማዕከል ለውጥ ለማድረግ የተገደደ ተቋም መገደዱን ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ ተማሪዎችና ሰራተኞች እንዳይበተኑና ተቋሙም ለከፋ አደጋ እንዳይጋለጥ ለኤጀንሲው በአፋጣኝ ማሳወቅ አለበት፡፡ ኤጀንሲውም በ1 ወር ጊዜ ውስጥ ለተቋሙ ጥያቄ ምላሽ መስጠት አለበት፡፡

2.2.7. ተቋሙ የካምፓስ ወይም የርቀት ቅርንጫፍ ማዕከል ለውጥ ለማድረግ ማቀዱን ለኤጀንሲው አስቀድሞ ሳያሳውቅ ለውጥ ያደረገ ከሆነ በንዑስ ተራ ቁጥር 2.2.1፣ 2..2.2፣ 2.2.3 ያሉት የቅጣት ደረጃዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

2.2.8. ኤጀንሲው ተቋሙን በተመለከተ የወሰደውን እርምጃ አስመልክቶ ለህዝቡ በሚዲያ ያሳውቃል፡፡

## <u>አንቀፅ 3</u>

ፈቃድ ባላገኙበት የትምህርት መስክ ስልጠና መስጠት ፡-

3.1. ያለምንም ቅድመ ማስጠንቀቂያ የዕውቅና ፈቃድ ያልተሰጠበት ፕሮግራሙ ይዘጋል፡፡

3.2. ይህ ተግባር በተከናወነበት ከተማ ተቋሙ በዚህ ፕሮግራም ለሁለት ዓመት በየትኛውም ካምፓሱ ወይም የርቀት ቅርንጫፍ ማዕከሉ ፈቃድና የፈቃድ እድሳት እንዳይሰጠው ዕግድ ይጣልበታል ፡፡

3.3. ተቋሙ የዕውቅና ፈቃድ ባላገኘ ስልጠና በሰጠበት መስክ የሰጠው ተምህርትና ማናቸውም ማስረጃ ተቀባይነት አይኖረውም

Ministry of Science and Higher Education, Federal Democratic Republic of Ethiopia

Federal Democratic Republic of Ethiopia, Higher Education Relevance & Quality Agency

3.4. ተቋሙ ለፈጠረው ችግር በወንጀልና በፍ/ብሄር ህግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡ይህንኑም የህግ ተጠያቂነት ኤጀንሲው ይፈፅማል/ያስፈጽማል፡፡

**<u>አንቀፅ 4</u>**

የዕውቅና ፈቃድን ሳያሳድሱ ሲሰሩ መገኘት

4.1 ተቋሙ የእውቅና ዕድሳት ጥያቄ እውቅናው ከማለቁ ከ6 (ስድስት) ወር በፊት አቅርቦ በኤጄንሲው በተሰጠ የጊዜ ገደብ ውስጥ ከኤጀንሲው ተገቢውን ምላሽ በወቅቱ ባላገኘበት ሁኔታ ስልጠናው ቢቀጥል ተጠያቂነት አይኖርበትም ፡፡

4.2 ከዚህ በላይ በንዑስ ተ.ቁ 4.1 ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ተቋሙ በራሱ ድክመት የዕውቅና ፈቃዱን ሳያሳድስ የሶስት ወር ግዜ ያሳለፈ እንደሆነ ለእውቅና ፈቃድ ዕድሳት የሚከፍለውን መደበኛ ክፍያ ከክፍያው 100% ተጨማሪ ቅጣት በመክፈል እንዲታደስለት ይደረጋል፡፡ የመጨረሻ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሠጠዋል፡፡

4.3 ከዚህ በላይ በንዑስ ተ.ቁ 4.2 ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ተቋሙ የዕውቅና ፈቃዱን ሳያሳድስ ስደስት ወር ያሳለፈ እንደሆነ የዕውቀና ፈቃድ እንዳልተሰጠው ተቆጥሮ ባልታደሰው ፕሮግራም ተቀብሎ ሲያሰለጥናቸው የነበሩ ተማሪዎችን ተመሳሳይ የእውቅና ፈቃድ ባላቸው ተቋማት በማዘዋወር ትምህርታቸውን እንዲያስጨርሳቸው ይደረጋል፡፡

**<u>አንቀፅ 5</u>**

በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተሰጠውን የደረጃ ስያሜ በማናቸውም ሁኔታ ለውጦ ሲገለገል የተገኘ ተቋም

5.1 ከኤጀንሲው ደብዳቤ በደረሰው በ10 ቀን ውስጥ ማስተካካያ በማድረግ ለኤጀንሲው ሪፖርት ያደርጋል

5.2 ህጋዊ ያልሆነ ስያሜውን በበራሪ ወረቀቶች፣ በማስታወቂያ ሰሌዳ ወይም በሌላ በማናቸውም ዘዴ ለህዝብ ገልጸ ከሆነ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ማስተባበያ በተመሳሳይ ሚዲያ ለህብረተሰቡ እንዲገልጽ ይገደዳል። ይህንን በተግባር ለመፈጸሙም በመረጃ የተደገፈ ሪፖርት ለኤጀንሲው ያቀርባል፡፡

5.3 ለዚህም ጥፋቱ ለአንድ ዓመት በማናቸውም ፕሮግራሞቹ ተማሪ እንዳይቀበል ይደረጋል፡፡

5.4 ከላይ በንዑስ ተ.ቁ 5.1፣ 5.2 እና 5.3 ላይ የተጠቀሱትን ተግባራዊ አለማድረጉ ሲረጋገጥ ተቋሙ እንዲዘጋ ይደረጋል፡፡

## አንቀፅ 6

በሚያሰለጥንባቸው ፕሮግራሞች በኤጀንሲው ከተፈቀደውና ከተወሰነላቸው ጊዜያቶች በማሳጠር እያስተማረ ያለ ወይም ያስመረቀ እንዲሁም አስፈላጊ የሆኑ የመመረቂያ መስፈርቶችን ያላሟላ ተማሪ ያስመረቀ በተጨማሪም በኤጀንሲው ተቀባይነት ያገኘውን ስርዓተ ትምህርትን ሳይከተል ትምህርት የሰጠ ተቋም

6.1. ከተቋሙ በዚህ መሰረት ተምሮ የተመረቀና የተሰጠ የት/ርት ማስረጃ በየትኛውም መልኩ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

6.2. ተቋሙ በዚህ መንገድ እየተማሩ ያሉ ወይም ትምህርታቸውን ያጠናቀቁ ተማሪዎች ቢኖሩት ወደ ተቋሙ ተመልሰው ስርዓቱ በሚፈቅደው መሰረት እንዲማሩና እንዲመረቁ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ አፈፃፀሙን በተመለከተ በኤጀንሲው ጥብቅ ክትትልና ቁጥጥር ይደረግበታል፡፡

6.3. ተቋሙ ይህንን ተግባር ለመጀመሪያ ጊዜ የፈፀመ እንደሆነ በፕሮግራሙ የትምህርት ርዝማኔ ያህል አዲስ ተማሪ እንዳይቀበል ይደረጋል፡፡ የመጨረሻ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያም ከኤጀንሲው ይሰጠዋል፡፡

6.4. ተቋሙ ይህንን ተግባር ደግሞ ሲፈጽም ከተገኘ ከስርዓት ውጭ ሲያስተምርባቸው የነበሩት ፕሮግራሞች እንዲዘጉ ይደረጋል፡፡ አዲስ ተማሪዎች እንዳይቀበልም የሶስት ዓመት ዕግድ ይጣልበታል፡፡

## አንቀፅ 7

ለአንድ ፕሮግራም የእውቅና ፈቃድ ወይም የእውቅና ፈቃድ እድሳት ወቅት ሊኖሩ የሚገቡ የቋሚና የኮንትራት ቅጥር የመምህራንን ቁጥርና የትምህርት ደረጃ ስብጥር ባላሟላ መልኩ ስልጠና ሲሰጥ የተገኘ ተቋም

7.1 በ45 ቀን ጊዜ ውስጥ ቅጥር በመፈጸም ለኤጀንሲው በመረጃ የተደገፈ ሪፖርት እንዲያቀርብ ይደረጋል፡፡ ለተፈጸመው ህገወጥ ተግባርም የመጨረሻ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፡፡

7.2. ተቋሙ ኤጀንሲው የሰጠውን ውሳኔ ተግባራዊ ለማድረግ ካልቻለ በተቋሙ ውስጥ በተጠቀሰው ፕሮግራም ሲማሩ የነበሩ ተማሪዎችን ሌላ እውቅና ወዳለው ተቋም አዛውሮ ትምህርታቸውን እንዲጨርሱ ይደረጋል፡፡ ተቋሙም በዛ ፕግራም የተሰጠው የእውቅና ፈቃድ ይሰረዛል፡፡

አንቀፅ 8

በትምህርት ሚኒስቴር ወይም በኤጀንሲው በየትምህርት ዘመኑ የሚተላለፉና ወቅታዊ የሆኑ የከፍተኛ ትምህርት መግቢያ መቁረጫ ነጥብን ወይም ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ማዕቀፍ ወደ ከፍተኛ ትምህርት መሸጋገሪያ መመሪያ የተደነገገውን የመግቢያ መስፈርት ያላሟሉ ተማሪዎችን ተቀብሎ የተገኘ ተቋም

8.1. ከህግ ውጭ የመዘገባቸውን ተማሪዎች ያሰናብታል፤

8.2. ተቋሙ ከሕግ ውጭ ምዝገባ ባካሄደባቸው የትምህርት ዘርፎች ለ3 (ሶስት) ተከታታይ አመታት ምንም ዓይነት ትምህርትና ስልጠና እንዳይሰጥ ይታገዳል፡፡

8.3. ኤጀንሲው በተቋሙ ላይ የተወሰደውን እርምጃ አስመልክቶ ለህዝብ በሚዲያ ይገልጻል፡፡

8.4. በዚህ መልክ የተገኙ የትምህርት መረጃዎች በአገር አቀፍ ደረጃ በቅጥር ፤ በአቻ ግመታ፣ በትምህርት ማስረጃ ማረጋገጫ፣ በሹመት፤ በምደባ ወዘተ ተቀባይነት አይኖራቸውም፡፡

8.5. ተቋሙ ይህንን ተግባር ደግሞ ከፈጸመ ተግባሩ የተፈጸመባቸው ፕሮግራሞች እና ካምፓስ ወይም የርቀት ቅርንጫፍ ማዕከል እስከ መጨረሻው እንዲዘጋ ይደረጋል፡፡

አንቀፅ 9

በወጭ መጋራት ያልታቀፉ ተማሪዎች በትራንስፈር ወይም በምረቃ ግዜ የሚያገኙአቸውን ኦፍሻል ትራንስክሪፕቶች ሳይቀበል ወይም በስድስት ወር ግዜ ውስጥ እንዲያሟሉ ሳያደርግ ተማሪ መዘገቦ የተገኘ ተቋም

9.1. ተቋሙ ተማሪው ከላይ በተገለጸው ግዜ ውስጥ ዶክመንቱን አለሚሟላቱን እንዳረጋገጠ ትምህርቱን እንዳይቀጥል የማድረግ ሃላፊነት አለበት፡፡ ነገር ግን ተቋሙ ተማሪውን ሳያሰናብት ከተገኘ ተማሪው በዛ የትምህርት መስክ እንዳልተማረ ተቆጥሮ በማንኛውም መልኩ ከተቋሙ የተሰጠ የትምህርት ማስረጃ ተቀባይነት እንዳይኖረው ይደረጋል፡፡

9.2. ተማሪው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ኦፍሻል ትራንስክሪፕት ለማቅረብ አለመቻሉ ከተረጋገጠ ተቋሙ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በማቅረብ ከኤጀንሲው ጋር በመነጋገር መፍትሄ አቅጣጫ እንዲሰጠው ሊያደርግ ይችላል፡፡

9.3. ተቋሙ ከዚህ ውጭ የመዘገባቸውን ተማሪዎች ያሰናብታል፤ ለዚህ ተግባሩም የመጨረሻ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ እንዲሰጠው ይደረጋል፡፡

9.4. ኤጀንሲው በተቋሙ ላይ የተወሰደውን እርምጃ አስመልክቶ ለህዝብ በሚዲያ ይገልጻል፡፡

9.5. በዚህ መልክ የተገኙ የትምህርት መረጃዎች በአገር አቀፍ ደረጃ በቅጥር ፣ በአቻ ግመታ፣ በትምህርት ማስረጃ ማረጋገጫ፣ በሹመት፤ በምደባ ወዘተ ተቀባይነት አይኖራቸውም፡፡

9.6. ተቋሙ ይህንን ተግባር ደግሞ ከፈጸመ ተግባሩ የተፈጸመባቸው ፕሮግራሞች እና ካምፓስ ወይም የርቀት ቅርንጫፍ ማዕከል እስከ መጨረሻው እንዲዘጋ ይደረጋል፡፡

## አንቀፅ 10

በወጭ መጋራት የታቀፉ ተማሪዎች በትራንስፈር ወይም በምረቃ ጊዜ የሚያገኙዋቸው ኦፊሻል ትራንስክሪብቶች መቀበልን የሚመለከተው ተቋም

በወጭ መጋራት ስርአት ውስጥ የታቀፉ ተማሪዎችን በተመለከተ ለኦፍሻል ትራንስክሪፕት የሚቀርቡ መረጃዎችን በተቋሙና በተማሪው መካከል በሚደረግ የውል ስምምነት የሚታሰብ ሆኖ ተማሪው የምረቃ ግዜው ከመጠናቀቁ በፊት ተገቢውን መረጃ ሟሟላቱን ተቋሙ ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ከዚህ ውጭ የሚሰጥ የትምህርት መረጃ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ ተሰጥቶም ከተገኘ ተቋሙ በህግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## አንቀፅ 11

በኤጀንሲው ከተፈቀደው የተማሪ ቁጥር በላይ መዝግቦ ማስተማር፣

11.1. ኤጀንሲው በሚያወጣው መስፈርት መሰረት ተቋማት እውቅና በጠየቁባቸው የትምህርት ዘርፎች ሊቀበሏቸው የሚችሉትን ተማሪዎች ቁጥር ካላቸው የግብአት አቅርቦት ጋር በተገቢው ሁኔታ በማመጣጠንና በመተመን የእውቅና ፍቃድ ይሰጣል፡፡

11.2. ተቋማት በተለያየ ምክንያት በመስኩ ከተፈቀደላቸው የተማሪ ቁጥር በላይ ቅበላ በሚያከናውኑበት ወቅት ተገቢውን ግብዓት ማሟላታቸውን ከማረጋገጥ በተጨማሪ በዚህ ረገድ የተደረገውን ለውጥ ለኤጀንሲው የተሟላ ሪፖርት በ4 ወር ግዜ ያቀርባሉ፡፡

11.3. ተቋማት በ6 ወር ግዜ ውስጥ አስፈላጊውን ግብዓት እንዲያሟሉ ይገደዳሉ፡፡ ኤጀንሲውም ከላይ የተመለከተው ለውጥ ትግበራ መሆኑን በየወቅቱ ያረጋግጣል፡፡

11.3. ተቋማት በንዑስ ተራ ቁጥር 11.1. 11.2 እና 11.3 ላይ በተመለከተው መሰረት ተግባራዊ አለማድረጋቸውን ኤጀንሲው ካረጋገጠ፡፡

11.4. ተቋሙ ከቁጥር በላይ የመዘገባቸውን ተማሪዎች ያሰናበታል፡፡

11.5. ይህን የፈፀመው ተቋምም በትምህርት መስኮቹ ለተከታታይ 2 ዓመታት ተማሪ እንዳይቀበል እግድ ይጣልበታል፡፡

## አንቀፅ 12

### የተማሪ መረጃ አያያዝ፣ አጠባበቅና አላላክን መመሪያ የጣሰ ተቋም

ማንኛውም ተቋም የተማሪዎቹን አካዳሚክ ታሪክ የሚሳዩ መረጃዎች ለምሳሌ ምዝገባ ማቋረጥ፣ ኤግዘምሽን፣ ትራንስፈር፣ የውጤት መግለጫ ሪፖርት ወዘተ የተመለከቱትን በአግባቡ የሚያሳዩና የተቋሙ የተለያዩ የስልጣን አካላት በተሰጣቸው የስልጣን ዕርከን መሰረት የወሰኗቸውን ውሳኔዎች በአግባቡ አደራጅቶ ማስቀመጥ አለበት፡፡የአዲስ ተማሪዎችን ዝርዝር ትምህርት በተጀመረ በ6 ወር ግዜ ውስጥ እንዲሁም የተመራቂ ተማሪዎችን ዝርዝር በ3 ወር ግዜ ውስጥ ለኤጀንሲው ማሣወቅ አለበት፡፡በተጨማሪም ኤጀንሲው ከተቋሙ የሚፈልጋቸውን ሌሎች መረጃዎች በተመለከተ አግባብ በሚባል የግዜ ገደብ ተገቢውን ምላሽ መስጠት ይገባዋል፡፡

ተቋሙ ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን በወቅቱ አለማቅረቡ ወይም አለመላኩ ሲረጋገጥ

12.1 በመመሪያው መሰረት ተገቢውን መረጃ አደራጅቶ በ30 ቀናት ውስጥ ሪፖርት እንዲያቀርብ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ከኤጀንሲው እንዲደርሰው ይደረጋል፡፡

12.2. በትዕዛዙ መሰረት ሳይፈጽም ከቀረ የመጨረሻ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ከኤጀንሲው እንዲደርሰው ይደረጋል፡፡

12.3. በመጨረሻው የፅሁፍ ማስጠንቀቂያው ግዜ ለማስተካከል ፈቃደኛ ካልሆነ ለ1 ዓመት የሚዘልቅ የአዲስ ተማሪ ቅበላ ዕግድ ይጣልበታል፡፡

## አንቀፅ 13

ኤጀንሲው የሰጠውን የእውቅና ፈቃድ በግልጽና ለተገልጋዩ ህብረተሰብ በሚታይ ሁኔታ በማስታወቂያ ሰሌዳው ላይ ያልለጠፈ ወይም ያላሳወቀ ተቋም ፡-

13.1. ተቋሙ ማስተካከያ እንዲያደርግ የጽሁፍ ትዕዛዝ ከኤጀንሲው ይሰጠዋል፡፡ በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረትም በ15 ቀን ውስጥ ማስተካከያ በማድረግ ለኤጀንሲው ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

13.2. በቁጥር 13.1 የተመለከተውን ተግባራዊ አለማድረጉ ሲረጋገጥ የመጨረሻ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፡፡

13.3. በተሰጠው የመጨረሻ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ መሠረት ማስተካከያ ያላደረገ ተቋም ኤጀንሲው ለተቋሙ በመስኩ የሰጠውን የእውቅና ፈቃድ ለአንድ ዓመት የተማሪ ቅበላ እንዳያደርግ ዕግድ ይጥልበታል፡፡

**አንቀፅ 14**

በእውቅናና እውቅና እድሳት ወቅት በተቋሙ የነበሩ ግብዓቶች በድንገተኛ ጉብኘት ጊዜ የታዩ አጓድሎ የተገኘ ተቋም

14.1 ቢያንስ በ3 ወር ግዜ ውስጥ የተጓደሉ ግብዓቶችን እንዲያሟላ ተቋሙ ይገደዳል፡፡ ተቋሙም ስለሟሟላቱ ለኤጀንሲው ሪፖርት ያድርጋል፡፡ ለፈጸመው ህገ-ወጥ ተግባርም የመጨረሻ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፡፡

14.2 ከላይ በተራ ቁጥር 14.1 በተጠቀሰው ግዜ ተግባራዊ አለማድረጉ ሲረጋገጥ የግብዓቱ መጓደል ተጽእኖ የሚያሳድርባቸው የትምህርት መስኮች እንዲዘጉ ይደረጋል፡፡ በመማር ላይ ያሉ ተማሪዎችም ወደ ሌሎች እውቅና ወዳላቸው ተቋማት እንዲዛወሩ ይደረጋል፡፡

14.3 ኤጀንሲውም ይህንኑ እርምጃ ለሕዝብ በሚዲያ እንዲገለጽ ያደርጋል፡፡

**አንቀፅ 15**

የትምህርትን ጥራት አደጋ ላይ በሚጥል መልኩ ተገቢውን መረጃ ከተቆጣጣሪ አካላት ክትትል ለመደበቅ ወይም ለማጥፋት ሲባል የሚደረጉ ህገወጥ ድርጊቶችን የፈፀመ ተቋም

15.1. ተቋሙ ማስተካከያ እንዲያደርግ የጽሁፍ ትዕዛዝ ከኤጀንሲው ይሰጠዋል፡፡ በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረትም በ30 ቀን ውስጥ ማስተካከያ በማድረግ ለኤጀንሲው ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

15.2. በቁጥር 15.1 የተመለከተውን ተግባራዊ አለማድረጉ ሲረጋገጥ የመጨረሻ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፡፡

15.3. በተሰጠው የመጨረሻ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ መሠረት ማስተካከያ ያላደረገ ተቋም ኤጀንሲው ለተቋሙ በመስኩ የሰጠውን የእውቅና ፈቃድ ለአንድ ዓመት የተማሪ ቅበላ እንዳያደርግ ዕግድ ይጥልበታል፡፡

# ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 4.1. ጥቆማን በተመለከተ

4.1.1. ማንኛውም ሰው በዚህ መመሪያ ውስጥ የተካተቱ መርሆዎችን የሚጻረር ጥፋት መፈጸሙን በማንኛውም መንገድ ካወቀ ወይም ከተመለከተ ጉዳዩን ለኤጀንሲው ሃላፊ ወይም ለህግ አገልግሎት ክፍል ማሳወቅ አለበት፡፡

4.1.2. የሚያቀርበው ጥቆማ እውነተኛ፣ ያልተዛባ፣ ከበቀል የጸዳ፣ አሳሳች ያልሆነና ምክንያታዊ በሆነ እምነት ላይ የተመሰረተ መሆን ይኖርበታል፡፡

4.1.3. ጥቆማ አቅራቢው ከማንኛውም በቀል እና ጥቃት የመጠበቅ መብት አለው፡፡

### 4.2. የመተባበር ግዴታ

4.2.1. ተቋማት ኤጀንሲው የሚፈልገውና የሚጠይቀውን መረጃና ሌላ ድጋፍ የመስጠት ግዴታ አለበት

4.2.2. ይህንን መመሪያ ለማስፈጸም በሚደረጉ ህጋዊ እንቅስቃሴዎች የክልል መስተዳድሮች ፣ የፍትህ አካላት ፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣መምህራንና የአስተዳደር ሰራተኞች ፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች ወላጆች እንዲሁም ሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡

### 4.3. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች

ይህንን መመሪያ ሚቃረን ማንኛውም መመሪያ የአስተዳደር ውሳኔ የአሰራር ልምድ በዚህ መመሪያ ውሥጥ የተጠቀሱ ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈጻሚነት አይኖረውም

### 4.4. የሽግግር ጊዜ ሁኔታዎች

ይህንን መመሪያ ለማስፈጸም በሚደረግ የተግባር እንቅስቃሴ በሽግግር ጊዜ ሊፈጸሙ የሚገቡ ናቸው ተብለው በሚለዩ ተግባራት ላይ ኤጀንሲው ዝርዝር የአፈጻጸም ሂደቶችንና ጊዜያቶችን በመለየት ለሚመለከታቸው አካላት ያሳውቃል፣ ተግባራዊነታቸውንም ይከታተላል፡፡

### 4.5 መመሪያውን ስለማሻሻል

ኤጀንሲው ይህንን መመሪያ ለማሻሻልም ሆነ አዲስ መመሪያ ለማውጣት ይችላል፡፡

### 4.6 መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከ ሚያዝያ 22 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

Ministry of Science and Higher Education
Federal Democratic Republic of Ethiopia

Federal Democratic Republic of Ethiopia
Higher Education Relevance & Quality Agency